GSS

የአለም አቀፍ ደረጃዎች ለአቅራቢዎች

# ሁሉም አቅራቢዎች የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው:-

HANES
Brands Inc

## የቅጥር ስራ ልምዶች፦

HanesBrands ሰራተኞችን በአግባቡ፣ በክብር እና በአክብሮት ለመያዝ ከፍተኛ ቁርጠኝነት አለው።

ይህንን ቁርጠኝነት ከሚጋሩ አቅራቢዎች ጋር የንግድ ሥራን እናደርጋለን።

አቅራቢዎች ሁሉንም አግባብነት ያላቸውን ህጎች እና ደንቦች እንዲታዘዙ እና ለሰዎች ሁሉ መሠረታዊ የሆኑ የሰብአዊ መብቶችን እንዲደግፉ እንጠይቃለን።

## የህፃናት ጉልበት ሥራ፡

አቅራቢዎች በሚንቀሳቀሱበት አገር ውስጥ በአካባቢው በሚያስገድደው የትምህርት እድሜን በመጣስ ወይም በሃገሪቷ ከሚሠራበት ሕጋዊ የቅጥር እድሜ ቤታች  ያሉ ግለሰቦችን አይቀጥሩም።

በተጨማሪም በማስታወቂያ ወይም በመገናኛ ዘዴዎች የተደገፉ በህጻናት የጉልበት መስፈርቶች የሚጠበቁ ህፃናት ተዋናዮች እና ሞዴሎች በስተቀር አሠሪዎች ዕድሜያቸው ከ 15 ዓመት በታች የሆኑ ሰራተኞች አይቀጠሩም።

## ካሳ፦

አቅራቢዎች ዝቅተኛውን የደመወዝ ክፍያ፣ የትርፍ ሰዓት ወጭዎች፣ አበል እና ጥቅማ ጥቅሞችን ጨምሮ ሌሎች አግባብነት ያላቸው የካሳ ሕጎች እና ደንቦችን ያከብራሉ።

አቅራቢዎች ቢያንስ በህግ የተጠየቀው ካሳ ወይም ወቅታዊውን የኢንደስትሪ ካሳ፣ የበለጠ የሆነውን ይከፍላሉ።

HanesBrands ሰራተኞች ሁሉ ትክክለኛውን ካሳ የማግኘት መብት እንዳላበቸው ይገነዘባል።

በተጨማሪም HanesBrands ተጨማሪ ሰራተኛ (ደመወዝ, ተጨማሪ ጉርሻዎች እና የአይነት ጥቅሞች፣ ትርፍ ጊዜን ሳይጨምር) ሰራተኞቹን መሰረታዊ ፍላጎቶች እንዲያሟሉ እና የተወሰነ ትርፍ የሚያስገኙ መሆን እንዳለባቸው ይገነዘባል።

አቅራቢዎች እንዲህ ዓይነቱን ትክክለኛ ደረጃ ያለውን ማካካሻ እንዲያቀርቡ እንመክራለን።

ይህ ግብ ካልተሟላ፣ አቅራቢዎች የሚያደርጉትን የማካካሻ ደረጃ በደረጃ እንዲይዙ ለማድረግ የሚረዱ ተገቢ እርምጃዎችን ለመውሰድ ከእኛ ጋር ይሰራሉ።.

## መድልዎ የሌለው፦

አቅራቢዎች በሰዎች በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በብሄር (የዘር)፣ በዕድሜ፣ በኃይማኖት፣ በአካል ጉዳት፣ በጾታ ዝንባሌ፣ በፆታ ማንነት፣ በውትድርና ነበርነት ሁኔታ ላይ ተመስርተው በቅጠር፣ ካሳ፣ እድገት፣ ስነ ስርዓት፣ ማቋረጥ ወይም ጡረታ፣ የጋብቻ ሁኔታ እና ማንኛውም ሌሎች የተጠበቁ ባህሪያት ወይም እምነቶች ላይ መድልዎ አያደርጉም።

ለሁሉም እኩል እድል የሚሰጡትን አቅራቢዎች HanesBrands የበለጠ ይደግፋቸዋል።

## አስገዳጅ የሰው ጉልበት፦

አቅራቢዎች የእዳ ማስመለሻ አገልግሎትን ጨምሮ ተያያዥነት ያላቸው፣ በእስር ወይን በውል አስገዳጅ ወይም ያለ ፈቃድ የጉልበት ሥራ አይጠቀሙም።

## የመደራጀት ነጻነት እና የህብረት ድርድር፦

አቅራቢዎች ሰራተኞች የመደራጀት መብታቸውን የመጠቀም መብት ያከብራሉ እና ይገነዘባሉ።

በተመሳሳይ ሁኔታ አቅራቢዎች ሠራተኞቻቸውን የህብረት ድርድርን የመምረጥና ያለመምረጥ መብታቸውን ይገነዘባሉ እና ያከብራሉ።

## ደህንነት እና ጤና፦

አቅራቢዎች ለሰራተኞቻቸው ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ የስራ ቦታን ያካሂዳሉ።

አቅራቢዎች ደህንነታቸው ያልተጠበቁ ድርጊቶችን እና ሁኔታዎችን በማስወገድ፣ ሰራተኞቻቸውን፣ ደንበኞቻቸውን እና አጠቃላይ ህዝቦችን ከጉዳት ለመታደግ ቁርጠኝነት መወሰድ አለባቸው።

በሚሚለከተው ሁሉ ይህ በቤቶች እና የመመገቢያ አገልግሎት መስጫዎች ላይ ይሠራል።

## የስራ ቦታ ጥቃት ወይም መጎሳቆል፦

አቅራቢዎች ሰራተኞችን አካላዊ፣ ቃላት፣ በጾታ፣ ወይም በስነ-ልቦና ወከባ ላይ አያነሳሱም፣ እንዲሁም ሰራተኞችን ለመቅጣት አካላዊ ቅጣት አይወስዱም።

## የስራ ሰዓታት፦

አቅራቢዎች የስራ ሰዓትን በተመለከተ በሚመለከታቸው ህጎች እና ደንቦች መገዛት አለባቸው።

ከተለመደው ሁኔታ ውጭ፣ ሰራተኞች በሕጋዊ ገደቦች ላይ ወይም ከ 48 መደበኛ ሰዓታት ሲደመር 12 ተጨማሪ ሰዓት በላይ በሳምንት ውስጥ ያነሰው ተወስዶ መሥራት የለባቸውም።

አቅራቢዎች ለሰራተኖች ከ 6 ተከታታይ የሥራ ቀናት በኋላ ቢያንስ 24 ተከታታይ ሰዓታት እረፍት መስጠት አለባቸው።

የትርፍ ሰዓት ሥራ በመደበኛነት መጠየቅ የለበትም እና በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት።

## አካባቢ፦

HanesBrands ዓለም አቀፍ መልካም የአካባቢ ጥበቃን በመጠቀም በአለም ዙሪያ ያለውን የአካባቢ ጥበቃ ጥራት ለመጠበቅ ያለውን ቁርጠኝነት ከሚጋሩት አቅራቢዎች ጋር የንግድ ስራ መስራትን ያምናል።

አቅራቢዎች በሁሉም የሚመለከታቸው የአካባቢ ጥበቃ ህጎች እና ደንቦች የሚገዙ ሲሆን ማናቸውንም ተያያዥ ያልሆኑ ልምዶችን ለማረም እቅዶችን ወይም መርሃግብሮችን በአፋጣኝ ያፀድቃሉ።

አቅራቢዎች ቆሻሻን/ተረፈ ምርቶችን ለመቀነስ እና የእነርሱ ስራዎች የሚያስከትለውን አካባቢያዊ ተፅእኖ ለመቀነስ እና ለማሳነስ ኃላፊነት ያለባቸው እርምጃዎችን ይወስዳሉ።

## ፀረ ሙስና፦

HanesBrands የውጭ ሙስና ተግባራት ሕግ እና የእንግሊዝ የጉቦ ዝውውር ህግን ጨምሮ በሁሉም የሚመለከታቸው ህጎች ሙሉ በሙሉ አጥብቆ ይተገበራል፣ እንዲሁም አቅራቢዎች በተመሳሳይ መልኩ እንዲፈጽሙ ያስገድዳቸዋል።

አቅራቢዎች የ HanesBrands የንግድ ስራ ፍላጎቶች ለማራመድ ጉቦ አይከፍሉም ወይም በሙስና ልማዶች አይሳተፉም።

ይህም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ለአካባቢው የህዝብ ባለስልጣኖች፣ ለፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ለፖለቲካ ሥልጣን እጩዎች ወይም በግል ግለሰቦች ወይም ሌሎች ግለሰቦች የመንግስት ባለስልጣናት እርምጃዎች ወይም ውሳኔዎች ላይ ተፅእኖ ለማድረግ ወይም ለመክፈል ገንዘብ ማዘዝ ወይም ለመክፈል ቃል መግባትን ያካትታል።



© 2022 Hanesbrands Inc.     ሁሉም መብቶች የተጠበቁናቸው።